



# ጎንደርን ለህጻናት
# የህጻናት የቱሪዝም
# መጽሐፍ



በሀገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን የተዘጋጀ

www.ethiopianorthodox.org

# ማውጫ

ቱሪዝም ምን ማለት ነው? ጎብኚ ማለትስ ታውቃላችሁ? ጎንደርንስ በደንብ ታውቋታላችሁ? በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አለላችሁ እሺ።


ሌላ ደግሞ.....

ትምህርት ስለሚወዱት አጼ ፋሲል........ገጽ 10

ለሰው የሚያዝኑት አጼ ዮሐንስ አንደኛ....ገጽ 12

ስለ ገናናው አጼ እያሱ..........................ገጽ 15

በገና ስለሚደረደሩት ንጉስ አጼ ዳዊት......ገጽ 17

ሙያ ስለሚያከብሩት ስለ ንጉስ ባካፋ...... ገጽ 19

ስለ ጥበበኛዋ ንግስት እቴጌ ምንትዋብ......ገጽ 21


ስለ ጎንደር መስህቦች፣ ስለ አጼ ፋሲል ግቢ መስህቦች፣ ስለጎንደር ቅርሶችና የተፈጥሮ ሀብቶች ያስተዋውቃችኋል። አንብቡ እሺ.....



## ቱሪዝም

ቱሪዝም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሲባልስ ሰምታችኋል? ቱሪዝም ማለት ፈረንሳይኛ ከሚባል ቋንቋ የተገኘ ነው። ፈረንሳይኛ የሚናገሩት ፈረንሳዮች ናቸው። በእነሱ ቋንቋ ቱሪዝም ማለት ተጓዥ ጎብኚ ማለት ነው።

ለምሳሌ እናንተ ትምህርት ሲዘጋ ከቤተሰቦቻችሁ ጋራ ወደ ሌላ አካባቢ ዘመድ ለመጠየቅ ስትሄዱ ለሄዳችሁበት አካባቢ ቱሪስቶች ናችሁ። በትምህርት ቤታችሁስ ጉብኝት ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? ከሄዳችሁ የሄዳችሁበት ቦታ ላይ ቱሪስት ናችሁ። ቱሪስት ማለት በአማርኛ ቋንቋ ጎብኚ ማለት ነው።




www.ethiopianorthodox.org

## ጉብኚ መሆን ምን ይጠቅማል?

እናንተ የት የት ጉብኝታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ምን አያችሁ? አያችሁ ስትጎበኙ እውቀትን ታገኛላችሁ። ለምሳሌ ትምህርት ቤት የተማራችሁትን በአካል ታዩታላችሁ።

የምትጎበኙበት ቦታ ከአካባቢያችሁና ከቤታችሁ የተለየ ስለሚሆን አዲስ ነገር ታያላችሁ። አዲስ ነገር በማየት እውቀት ታገኛላችሁ፤ አዲስ ነገር ደግሞ ደስ ይላል። መንፈሳችሁ ይታደሳል። መጎብኘት ደስ ይላል አይደል?





## የሚጎበኙ ቦታዎች ምን ምን እንደሆኑ ታውቃላችሁ?

የተፈጥሮ ሀብቶች ይጎበኛሉ። የተፈጥሮ ሀብቶች የምንላቸው ተራሮች፣ ሜዳዎች፣ ሐይቆች፣ የዱር እንስሳትና ዛፎች ናቸው። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ ቅርሶች ይጎበኛሉ። ቅርሶች የዱሮ ሰዎች የሰሯቸው ቤቶች፣ ቤተ ክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ መንገዶችና ድልድዮች ናቸው። የዱሮ ሰዎች የተጠቀሙባቸውም እቃዎች ተቀምጠው ይጎበኛሉ። ለምሳሌ የንጉሶች ልብስ፣ የጦር መሳሪያቸው፣ አልጋቸው፣ የቤታቸው እቃ፣ መጻህፍቶቻቸው የመሳሰሉት ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

# ጎንደር

ጎንደር የድሮ ከተማ ናት። በድሮ ጊዜ በሁሉም ቦታ ከተማ አልነበረም። የጎንደር እድሜ ብዙ መቶ ዓመት ነው። ሶስት መቶ ዓመት ልደቷ አልፎአል። የፋሲል ግንብ፣ የፋሲል መዋኛ እና ሌሎች ብዙ ቤቶች ብዙ ዓመታቸው ነው። ብዙ ዓመታቸው ስለሆነ ቅርስ ሆነዋል።







# ጎንደር የዓለም ቅርስ መሆኗን ታውቃላችሁ?

ጎንደር የምትገኘው በአማራ ክልል ነው። ድሮ ጎንደር እንደ አዲስ አበባ የሀገራችን ዋና ከተማ ነበረች። ያኔ የተሰራው የፋሲል ግንብ በጣም ያምራል። ፈረንጆች ሳይቀር ደስ ብሎአቸው ይጎበኙታል። በእነሱ ሀገርም እንደዚህ ዓይነት ግምብ ቅርስ ነው። የፋሲል ግምብን ፈረንጆች ሲጎበኙት ኢትዮጵያውያን ጎበዝ ናቸው ይህንን የመሰለ ህንጻ ሰርተዋል ብለው ያደንቁናል።

የፋሲል ግምብ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚያኮራ ነው። ግምቡ ቆንጆና አስደናቂ ስለሆነ ዓለም ሁሉ ፈረንጆችም ጭምር ይኮሩበታል። የዓለም ቅርስ የሆነውም ለዚህ ነው። ይህንን ግምብ የሰሩት ንጉሶች ይህንን ባይሰሩ ግን እኛን ለማየት ፈረንጆች አይመጡም። አያችሁ የግምቡ መሰራት ያለው ጥቅም፤ እነማን እንደሰሩት ታውቃላችሁ? በዚህ መጽሐፍ ላይ አሉ አንብቡት እሺ.



www.ethiopianorthodox.org

## ትምህርት የሚወዱት አጼ ፋሲል....

በድሮ ጊዜ አጼ ፋሲል የሚባሉ ንጉስ ነበሩ። የአጼ ፋሲል አባትም ንጉስ ናቸው። ስማቸው አጼ ሱሲኒዮስ ይባላል። በድሮ ጊዜ ንጉስ ሲሞት ልጁ ንጉስ ይሆንና ሀገሩን ያስተዳድራል። አጼ ፋሲል በልጅነታቸው ጎበዝ ተማሪ ነበሩ። ብዙ ትምህርት ተምረዋል። ከታላላቆቻቸው ታሪክ እየሰሙ አደጉ። ማንበብ ደግሞ ይወዳሉ።


አጼ ፋሲል ሌላ ስማቸው አዳም ሠገድ ይባላል። ሠው ሁሉ የሰገደላቸው ማለት ነው። የዛሬዋን ጎንደር ከተማ ዋና ከተማቸው አደርገው መሠረቱ። ትልቅ ቤተ መንግስትም አሠሩ። ይህ ቤተ መንግስት ፋሲል ግምብ ይባላል። ፋሲል ግምብ ሰፊ ግቢ አለው። ዙሪያውንም በግምብ ታጥሯል። አስራ ሁለት በሮች አሉት። አጼ ፋሲል ራሳቸው የሚወጡበትና የሚገቡበት በር ጃንተከል በር ይባላል።





ለአጼ ፋሲል የሚቀርቡዋቸው ጓደኞች ደግሞ በወንበር በር ይገባሉ ይወጣሉ። ጦርነት ላይ ወታደሮቹን የሚያዙት አለቆች አዛዥ በር በሚባለው በር ነው የሚወጡትና የሚገቡት።

ሌሎቹ በሮች እቃ ግምጃ ቤት በር፣ ቀጭን አሽዋ በር፣ ፈረስ በር፣ እምቢልታ በር፣ ኳሊ በር፣ እንኮዬ በር፣ ተዝካሮ በር፣ አደናግር በር፣ ርግብ በር ይባላሉ። በድሮ ጊዜ ማንም ሰው በአገኘው በር አይገባም ነበር። ሁሉም ወደ ቤተ መንግስቱ የሚገባው በተፈቀደለት በር ነው።



አጼ ፋሲል ያስገነቡት ቤተ-መንግስት



www.ethiopianorthodox.org

አጼ ፋሲል ጎበዝና መልኩ ቆንጆ የሆነ ፈረስ ነበራቸው። የፈረሳቸው ስም ደግሞ ዞብል ይባላል። ዞብል ሲሞት ትልቅ ቤት በግምብ አሰርተው እዛ ውስጥ ቀብረውታል። ሌላው ደግሞ ጥምቀት የሚከበርበት ትልቁ መዋኛ አጼ ፋሲል የሰሩት ነው። ብዙ ውሃ ይይዛል። ጎብኚዎችም የአጼ ፋሲልን ግምብ ይጎበኙታል። አጼ ፋሲል ንጉስ የሆኑት 24 ዓመት ነው።




አጼ ፋሲል ያስገነቡትና በየዓመቱ ጥምቀት የሚከበርበት መዋኛ ግንብ





## ለሰው የሚያዝኑት አጼ ዮሐንስ አንደኛ

አጼ ፋሲል ሲሞቱ የነገሱት ልጃቸው አጼ ዮሐንስ ናቸው። በሀገራችን አጼ ዮሐንስ የሚባሉት የመጀመሪያ ንጉስ የአጼ ፋሲል ልጅ ናቸው። ሰዎች አጼ ዮሐንስ አንደኛ ይሉዋቸዋል። አጼ ዮሐንስ አንደኛ የሚባሉት እኚህ ንጉስ ደግ ናቸው። ለሰው ሁሉ ያዝናሉ። ደግ ስለሆኑም ሰው ሁሉ ጻድቁ ይላቸዋል። ጻድቅ ማለት ጥሩ ስራ የሚሰራ መልካም ነገር የሚያደርግ ማለት ነው።



አጼ ዮሐንስ ያስገነቡት ቤተ-መንግስት



www.ethiopianorthodox.org

ከእለታት አንድ ቀን አንዲት አህያ የቤተ መንግስቱን አጥር ስትታከክ ንጉሱ ተመለከቷት:: የአህያዋ ባለቤት ብዙ ሸክም እያሸከማት አህያዋ ጀርባዋ ቆስሎ ነበር:: አጼ ዮሐንስም ሲመለከቱ አዘኑ፤ የአህያዋን ባለቤትም ጠርተው አህያዋን አስታሞ እንዲያድናት አስጠነቀቁ:: ከዚያን ጊዜ በኋላ ሁሉም ሰው ጀርባው የቆሰለውን አህያውን እንዳያሸክም አዘዙ:: አጼ ዮሐንስ አንደኛ አባታቸው ግምብ ቤት የሰሩበት ፋሲል ጊቢ ውስጥ ትልቅ ቤት አሰሩ:: ያሰሩት ቤት የፍቅር አዳራሽ ይባላል:: አጼ ዮሐንስ አንደኛ ጸሎት ያዘወትሩ ነበር:: ከስልጣናቸውም ተደብቀው ጠፍተው ገዳም ገቡ:: አጼ ዮሐንስ እያሱ የሚባል ልጅ ነበራቸው::





## ገናናው አጼ እያሱ

የአጼ ዮሐንስ አንደኛ ልጅ የነበሩት አጼ እያሱ አባታቸው ገዳም ሲገቡ እንደ አባታቸው ንጉስ ሆነው ተመረጡ:: አጼ እያሱም ቤት ያሰሩት እዛው አጼ ፋሲል ጊቢ ውስጥ ነበር:: የቤተ መንግስታቸው ስም እልፍኝ ይባል ነበር:: አጼ እያሱ ሩቅ ድረስ እየሄዱ ጦርነት ያደርጉ ነበር:: የሚያስተዳድሩትም ሀገር በጣም ሰፊ ነበር:: አሁን በሀገራችን እንዳለው ህገ መንግስት በዚያን ዘመን የነበረው ህግ ፍትሐ ነገስት ይባላል::



አጼ እያሱ ያስገነቡት ቤተ-መንግስት



www.ethiopianorthodox.org

አጼ እያሱ ፍትሐ ነገስት የሚባለውን መጽሐፍ እንደገና ተሻሽሎ እንዲጻፍ አደረጉ:: አጼ እያሱ ግብር የሚሰበሰብበትን ዘዴም ፈጥረዋል:: ነጋዴዎች አላግባብ ግብር እንዳይከፍሉም አደረጉ:: በጎንደር ከተማ ከሚገኙ ታሪካዊ ስፍራዎች አንዱ የሆነው የደብረ ብርሐን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ያሰሩት አጼ እያሱ ናቸው:: እውቀታቸው ከፍተኛ ነበር:: ዛሬ ሳውና ባዝ የሚባለውን ስልጣኔ የሚተካከል የወይባ መታጠኛ ግንብ ቤትም ገንብተዋል:: አጼ እያሱ እንዳአባታቸው ሁሉ ዘውዳቸውን አውልቀው ገዳም ገቡ::






# በገና ደርዳሪው ንጉስ አጼ ዳዊት 3ኛ

በገና በጣም የሚወደድ ባለ ክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ነው:: በገና የሚጫወት ሰው በገና ደርዳሪ ይባላል:: አጼ ዳዊት ሶስተኛ በገና በመደርደር/ በመጫወት/ ይታወቃሉ:: አጼ ዳዊት 3ኛ እንደነገሱም መጀመሪያ ያሰሩት ህንጻ እጅግ የሚደንቅ ቤተ ተውኔት ነው:: ይህ የቤተ ተውኔት ግንብ የተገነባው በፋሲል ግቢ ውስጥ ነው::

የአድባር በገድ ዳዊት ይባል ግንብ
1716-1721



አጼ ዳዊት ያስገነቡት ህንጻ



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ተውኔት ማለት ቴያትር ወይም ትእይንታዊ ዝግጅት የሚቀርብበት ማለት ነው። የቴያትር ቤት ግንባታም የጀመሩት ንጉስ አጼ ዳዊት 3ኛ ናቸው።

አጼ ዳዊት 3ኛ የአጼ ኢያሱ ልጅ ናቸው። አባታቸው ያሰሩት የደብረ ብርሃን ስላሴ ድንቅ ህንጻ በእሳት ሲቃጠል መልሰው ቆንጆ አድርገው አሰርተውታል። በአጼ ዳዊት 3ኛ ዘመን ታዋቂ ከሚባሉት ጥበበኞች አንዱ ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ይባላል። ይህ ሰው በጣም ቅኔ አዋቂና ጠቢብ ነው። አጼ ዳዊት 3ኛም ከሁሉም አብልጠው ይወዱት ነበር። ጥበብንና ጥበበኞችን የሚወዱት ንጉስ ዳዊት ስስተኛ አምስት ዓመታትን ከነገሱ በኋላ በበሽታ ታመመው ሞቱ።




ጎንደርን ለህጻናት

## መጽ አክባሪው ንጉስ

### አጼ በካፋ

አጼ በካፋ ከጎንደር ነገስታት አንዱ ናቸው። ገና በልጅነታቸው መጻህፍትን ያነቡ ነበር። ከሚያነቡት መጻህፍት ባገኙት እውቀትም መመራመር የሚወዱ ናቸው። አጼ በካፋ የአጼ ዳዊት 3ኛ ወንድም ናቸው። በድሮ ጊዜ የነገስታቱን ስልጣን የሚሻሙ ተብለው የሚጠረጠሩ የነገስታት ቤተሰቦች ወህኒ አምባ የሚባል ሩቅ ቦታ ተገልለው እንዲቀመጡ ይደረጋል። አጼ በካፋም ወህኒ አምባ ገብተው እንዲቀመጡ ተደረገ።



አጼ ዳዊት ያስገነቡት ህንጻ



www.ethiopianorthodox.org

አጼ ባካፋ የንጉሰ ነገስትነቱን ዘውድ የጫኑት ወህኒ አምባ እያሉ ነበር። አጼ ባካፋ እንደነገሱ አራሽ ይረስ...ነጋዴ ደግሞ ይነግድ... አናጢ....ቤት ሰሪ....ብረትና እንጨት ሰሪም በሙያው ይስራ ሐሜተኛና ወሬኛ አልፈልግም አሉ። ሰው ሁሉ በንጉስ ሀሳብ ደስ አለው። አጼ ባካፋ በራሳቸው ሀሳብ በውሀ ላይ የሚሄድ መርከብ ሰሩ። ለሀገራቸው እውቀት ትኩረት የሚሰጡት የትኛውንም ሙያ የሚያከብሩት አጼ ባካፋ ተወዳጅ ነበሩ።





# ጥበበኛዋ ንግስት
# እቴጌ ምንትዋብ

በጎንደር ከነበሩት ሴት ነገስታት መካከል አንዷ እቴጌ ምንትዋብ ይባላሉ። እቴጌ ምትንትዋብ እጅግ ጥበበኛ ንግስት ነበሩ። ብልህና በሳል ሴት እንደሆኑ ይነገራል። እቴጌ ምንትዋብ በአጼ ፋሲል ጊቢ ያሰሩት ቤተ መንግስት እጅግ በጣም ውብ ነው። መልኩ ያማረ እና በጌጣጌጥ ያሸበረቀ ግንብ ነው።

በጎንደር ቆይታቸውም ከነገስታቱ እኩል ስማቸው የገነነ ነበረ። በመጨረሻ ግን ከጎንደር ከተማ መሀል ራቅ ብለው ቁስቋም ከተባለ ተራራማ ቦታ ላይ እጅግ ውብ ቤተ ክርስቲያን አሰሩ። የቤተክርስቲያኗ ስም ቁስቋም ይባላል። በዚህ ስፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ የቆሎ ትምህርት ቤትን በዘመናዊ መልኩ አደራጅተው ተማሪዎችን እንደየትምህርት ደረጃቸው ማበረታት ጀመሩ።



www.ethiopianorthodox.org

## የአጼ ፋሲል ጊቢ ታሪካዊ መስህቦች

የአጼ ፋሲል ግቢን መጀመሪያ የሰሩት አጼ ፋሲል ናቸው:: ከእሳቸው በኋላ ስድስት ንጉሶች ቤተ መንግስት ሰርተዋል:: ሁሉም የሚገኙት አጼ ፋሲል ግቢ ነው:: ግቢው ውብና አረንጓዴ ነው:: በድሮ ጊዜ በጊቢው ውስጥ አንበሶች ይኖሩ ነበር:: የአንበሶቹ ቤት ዛሬም አለ::
ሌላው የአጼ ፋሲል መዋኛ የጎንደር ታሪካዊ ቅርስ ነው:: መዋኛው ሰፊ ስለሆነ የሚይዘው ውሃ ብዙ ነው:: የሚገኝበት ግቢም በእጽዋት ያሸበረቀ በመሆኑ ደስታን ይፈጥራል:: በየዓመቱ ጥምቀት የሚከበረው በዚህ መዋኛ ግቢ ነው:: መዋኛው ውሃ ይሞላና ሰዎች ገብተው ይዋኙበታል:: ወደ ውስጥ ትልቅ ጉድጓድ ስለሆነ ዋና የማይችል ሰው ወይም ህጻናት ቢገቡ ያሰምጣቸዋል::





## የጎንደር መንፈሳዊ ቅርሶች

በጎንደር ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ይገኛሉ:: ሁሉም ታሪካዊና የዱሮ ናቸው:: በተለየ ደብረ ብርሃን ስላሴ የሚባለው ቤተ ክርስቲያን እንደ ፋሲል ግምብ ያምራል:: ፈረንጆች በጣም ይደነቁበታል:: ረጅም እድሜ አለው:: የውስጡ ግድግዳ በጣም በሚያስደንቁ ስዕሎች ያሸበረቀ ነው::
ሌላው የጎንደር መንፈሳዊ መስህብ የቁስቋም ቤተ ክርስቲያንና አካባቢ ሲሆን እርሱም በንገስታቱ ጊዜ የተሰራ ነው:: በውስጡ በርካታ ቅርሶችን የያዘ ሙዚየም ይገኝበታል::
የጎንደር የመጀመሪያው መስጊድ አዲስ ዓለም በሚባለው አካባቢ የሚገኘው የአዲስ ቀዳም መስጂድ ነው:: ይህ መስጂድ እስላማዊ መንፈሳዊ መስህብ ነው::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## ተፈጥሮአዊ መስህቦች
## የጃን ተክል ዋርካ

ጃን ማለት ጃንሆይ ንጉስ ማለት ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ንጉሶች በአጭር ቀን [illegible] ደምቆ ይበራል፡፡ [illegible] እንደማለት ነው፡፡ [illegible] ፋሲል ጊዜ ዋናው በር ፊት ለፊት የሚገኘው ግዙፍ የዋርካ ዛፍ ጃን ተክል ይባላል፡፡ ንጉስ የተከለው ማለት ነው፡፡
ጃን ተክል ዋርካ ሰፊ ጥላ ያለው ሲሆን የጎንደር ከተማ መለያ ከሚባሉት አንዱ ነው፡፡ ጥላው ስር ሰዎች ይዝናናሉ፡፡ ዋርካው በድሮ ጊዜ አጼ ፋሲል ቤተ መንግስታቸውን ሳይሰሩ ድንኳን ተክለው በስሩ ያርፉበት ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት በጎንደር ከተማ ከጃን ተክል ሌላ በዙ [illegible] አካባቢ ይገኛሉ፡፡ ሁሉም ብዙ ዓመት የኖሩ ናቸው፡፡





## ጎሃት ተራራ

ጎንደር ከተማ ከፍተኛው ስፍራ ጎሃት ተራራ ይባላል፡፡ እዚህ ተራራ ላይ ወጥተው ጎንደርን በደንብ መመልከት ይቻላል፡፡ ተራራው አናት ላይ ጎሃ የሚባል ቅንጡ ሆቴል አለ፡፡ የጎንደር ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ ጣቢያም የሚገኘው እዚሁ ተራራ ላይ ነው፡፡

## አንገረብና ቀሀ ወንዞች

ጎንደር ላይ የሚገኙት ዋና ዋና ታዋቂ ወንዞች ሁለት ናቸው፡፡ አንገረብና ቀሀ ይባላሉ፡፡ አንገረብ ወንዝ ተገድቦ ይጠራቀምና ለጎንደር ከተማ መጠጥ ውሃ ሆኗል፡፡

ጎንደርን ለህጻናት

# ተፈጸመ

በቅርብ ቀን
የዓለም ቅርሶችን ለህጻናት

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org